36

8 5 20/02/2018
20/1/2007

732/2013

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development
Housing & Construction

ለኮርፖሬት ሃብት ሥራ አመራር ቢሮ

ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣

የ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ፎረም የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 36/2007 ሆኖ ከመስከረም 19 ቀን 2007 ዓ/ም ጀምሮ የጸደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሰረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የጸደቀው 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ፎረም አብይ ኮሚቴ
- ለ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ፎረም የቴክኒክ ኮሚቴ
- ለፋይናንስ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ሕግ መምሪያ
- ኦዲት መምሪያ

ከ/ል/ቤ/ኮ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማት፣ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT, HOUSING & CONSTRUCTION

የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም

Ethiopian Cities' Forum

# 6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይናንስና ሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 732/2013

መስከረም 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ


| | ገፅ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 2 |
| 2. አጭር ርዕስ | 2 |
| 3. ትርጓሜ | 3 |
| 4. የመመሪያው ዓላማ | 3 |
| 5. የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች | 3 |
| 6. ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሚተላለፈውን የሥራ ማስኬጃ ሂሣብ በተመለከተ፣ | 7 |
| 7. የግዢ መመሪያ መርሆዎች፣ | 7 |
| 8. የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፣ | 9 |
| 9. የፋይናንስና የሎጀስቲክስ አቅርቦት ሥራዎች የሚያስተባብር ኮሚቴ፣ | 9 |
| 10. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች፣ | 9 |
| 11. የቢሮ ዝግጅት፣ | 10 |
| 12. የመመዝገቢያ ክፍያ፣ | 11 |
| 13. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል፣ | 11 |
| 14. ከእስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፣ | 11 |
| 15. ሂሣብ ማስመርመር፣ | 12 |
| 16. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ፣ | 12 |


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማት ፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ የከተማ ነዋሪዎችንና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በማጠናከር መልካም ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በማስፋፋት የከተማ ልማት ፖሊሲውን፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ትግበራና ስኬት ማፋጠን ይቻል ዘንድ አመታዊ የከተሞች ሳምንት የተሰየመ ሲሆን፣ በዚሁ መነሻነት ላለፉት አምስት አመታት በየዓመቱ በተለያዩ ከተሞች የተካሄደ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ 6ኛዉ የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በሚል በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር በህዳር ወር 2007 ዓ.ም ይከበራል፡፡

ማንኛውም ተቋም የተሰጠውን ተግባርና የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ ሊያከናውን የሚችለው የተጠናከረ የገቢ ምንጭና በትክክል የተደራጀ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ስልት ሲኖረው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ የተደራጀና የተጠናከረ የፋይናንስና አቅርቦት አመራር ሲባል አንድ ተቋም የሚሰበሰበውን ገቢ፣ የሚያወጣውን ወጪና አቅርቦት እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውለው የሚከተለው የአሠራር ስልት ማለት ነው፡፡ ለዚህም የፋይናንስ ዕቅድና የፋይናንስ አያያዝ መመሪያዎችን እንዲሁም የአቅርቦት አፈጻፀም መመሪያ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ አመቺ ስልት መቀየስ፣ የተሟላና ተገቢ ይሆን የሒሳብና የአቅርቦት መዝገብ አያያዝና ሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም 6ኛውን የኢትዮጵያ የከተሞች ፎረም ዝግጅት በአግባቡ ለማካሄድ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በኃላፊነት እንዲመራ የተደራጀ ኮሚቴና የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ሥራቸውን ሲያከናውኑ የሚፈለግባቸውን ተግባር ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ከዚህ አኳያ የሚያከናውኑትን የዕለት ተዕለት ሥራ በአግባቡ ለማከናወን የሚረዳ የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡ በዚህም መሠረት ይህ አጭር የፋይናንስና ሎጂስቲክ የአቅርቦት አሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም የፋይናንስና የሎጂስቲክ አቅርቦት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 732/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

3. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

ሀ. "ገቢ/መዋጮ" ማለት ለስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅት ማከናወኛ ከመመዝገቢያ፣ ከድንኳን ኪራይ፣ ከስፖንሰሮች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሰበሰብ ነው።

ለ. "ወጪ" ማለት ከስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ሥራ ጋር በተገናኘ በተገቢው አካል ሲፈቀድ የሚፈፀም ክፍያ ነው።

ሐ. "ከተማ አስተዳደር" ማለት ስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ላይ የሚሳተፉ ከተሞች ናቸው።

መ. "የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር" የስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም እንዲያስተናግድ የተመረጠ ከተማ ነው።

ሠ. "አቅርቦት" ማለት ለስድስተኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በዓል አከባበር የሚውል ማንኛውም አይነት በግዥ፣ በስጦታ እና በትውስት የሚቀርብ ቁሳቁስ እና አገልግሎት አቅርቦት ነው።

ረ. "የበላይ አመራር" ማለት ሚኒስትሩ ወይም ሚኒስትር ደኤታዎች ናቸው።

4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የስድስተኛውን የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲቻል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመሰብሰብ፣ ግዥ ለመፈፀም፣ በአግባቡ ክፍያ ለመፈፀም፣ ተገቢውን ምዝገባ በማካሄድ ሂሣቡን ለማስመርመር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ነው።

5. የፋይናንስ መመሪያ መርሆዎች

1) ተቀባይነት ባላቸው የፋይናንስ አሠራር መርሆዎች፣ በሕግና በመንግሥት መመሪያዎች መሠረት ከ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም አከባበር ጋር በተያያዘ ያለውን ሂሣብ መዝግቦ በአግባቡ መያዝ፣ ገቢዎችን መሰብሰብ እና በጥንቃቄ እንዲያዝ ማድረግና ወጪዎችን መክፈል፣ ለሦስተኛ ወገን ተጠቃሚዎች የሚውሉ መደበኛና ልዩ የሒሳብ መግለጫ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና ማስመርመር ከፋይናንስ አንፃር የሚከናወኑ አበይት ተግባራት ናቸው።

2) ከዚህም በተጨማሪ የከተሞች ፎረም ፋይናንስ ከማንቀሳቀስ አኳያ የሚከተሉትን የባንክ ሂሳብ እና የፋይናንስ አሠራር መርሆዎችን መከተል ይገባል።

ሀ/ የከተሞች ፎረምን ለማካሄድ ከተለያዩ አካላት የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከዚህ በታች በተመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚገለገልበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር ገቢ ሆኖ ሥራ ላይ ይውላል።

"በከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የከተማ ፕላን፣ ዕዳትና ውበት ማስተባበሪያ ቢሮ ስም በተከፈተው የሒሳብ ቁጥር 1000000985027 ወይም 017153095060 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ"

ለ/ በዚህ የባንክ ሒሳብ ቁጥር ከ5ኛው የከተሞች ሳምንት ተራፊ የገንዘብ መጠን እና ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ከተለያዩ አካላት ለከተሞች ፎረም ዝግጅት ገቢ የተደረገው ገንዘብ ለእዚሁ ዓላማ ይውላል።

ሐ/ የባንክ ሂሣቡን ለማንቀሳቀስ የሚረዱ የቼክ ጥራዞችን የባንክ ሂሣብ እንቅሳቃሽ በሆኑ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጋራ ፈራሚዎች ለባንኩ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል።

መ/ በየወሩ የባንክ ሂሣብ እንቅስቃሴ መግለጫ ሪፖርት (Bank Statement) ሂሣቡ ከተከፈተበት ባንክ በማምጣት ሂሣቡ ከምዝገባው ጋር መታረቅ ይኖርበታል (Bank Reconciliation)።

3) የቼክ ፈራሚዎች አደረጃጀት በበጀት አመቱ በስራ ላይ ባለው የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር አሰራር የፊርማ ውክልና መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

4) የቼክ ጥራዞች አያያዝና የክፍያ አፈጻጸም፣

ሀ/ የከተሞች ፎረምን ሂሳብ ለማንቀሳቀስ ከባንክ የተሰጡ የቼክ ጥራዞች በአግባቡ መቀመጥ ይገባቸዋል።

ለ/ ለእያንዳንዱ የቼክ ወጪ የክፍያ ማዘዣ መዘጋጀት አለበት።

ሐ/ ቼኮች በሥራ ላይ የሚውሉት በተሰጣቸው የቁጥር ቅደም ተከተል መሠረት ብቻ መሆን አለበት።

መ/ ጉርድ ቼኮችን የያዙ ጥራዞች (ያለቁ ቼኮች) የሂሣብ ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በሚመደበው በክፍያና ሂሣብ ማወራረድ ከፍተኛ ኦፊሰር እጅ ሊቀመጡ ይገባል።

ሠ/ ክፍያ የተፈፀመባቸው የቼክ ቁጥሮችን የያዙ የክፍያ ማዘዣዎች በሂሣብ መዝገብ /IBEX/ ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

ረ/ ክፍያ የተፈጸመባቸው ተጎራጅ ቼኮች በኦዲተር ሲጠየቁ እንዲቀርቡ ይደረጋል።

5) የገቢ መዋጮ ሂሳብ አያያዝ፣

ሀ/ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ውስጥ የግለሰብ ገንዘብ ገቢ ሊደረግ አይችልም።

ለ/ የክፍያ ቀናቸው ያልደረሰ ወይንም ያለፉ ቼኮችን መቀበል አይፈቀድም።

ሐ/ የግለሰብ ቼኮችን መቀበል የሚቻለው ግለሰቡ በባንክ ሂሣቡ ውስጥ ገንዘብ ያለው መሆኑን ባንኩ ሲያረጋግጥ ብቻ ነው። በሌላ በኩል በCPO መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበን መዋጮ ገቢ ማድረግ ይቻላል።

መ/ በጥሬ ገንዘብ የተሰበሰቡ ገቢዎች በተቻለ መጠን በዕለቱ ባንክ መግባት ይኖርባቸዋል።

ሠ/ ገቢዎችም ሆኑ ወጪዎች በዕለቱ መመዝገብ አለባቸው።

ረ/ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በአግባቡ መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

ሰ/ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኞች ተከታታይ ቁጥር ሊኖራቸው ይገባል።

ሸ/ ጥሬ ገንዘብ እንዲይዝ የተመደበው ሰው ገንዘቡን በአግባቡ ስለመቀበሉ፣ ስለማስቀመጡና ስለመክፈሉ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ ይሆናል።

ቀ/ ገንዘብ ሰብሳቢውና የሂሣብ መዝገብ የሚይዘው ሰው የተለያየ መሆን ይኖርበታል።

በ/ በየዕለቱ የሚሰበሰበው ገንዘብ ሳይቀነስ በዕለቱ ባንክ እንዲገባ መደረግ ይኖርበታል።

ተ/ አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወይም ውክልና ከተሰጠው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ከተሰበሰበ ገቢ ላይ ክፍያ መፈፀም አይቻልም።

ቸ/ በእጅ የሚያዘው ጥሬ ገንዘብ በተቻለ መጠን አነስተኛ ብር 40,000.00 /አርባ ሺህ/ መሆን ይኖርበታል።

ኘ/ የሠራተኛ ወገን ወይንም የግል ገንዘብ ከዚህ ሂሣብ ጋር መቀላቀል አይኖርበትም። ሆኖም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያንቀሳቅሳቸው ፕሮጀክቶች ገንዘብ ገቢ ሲደረግ በተቀፅላ ሌጀር መለየት ይኖርበታል።

6) ክፍያን በተመለከተ አጠቃላይ መርሆዎች፣

ሀ/ የክፍያው ምክንያት ምንም ዓይነት ቢሆን ለክፍያው መነሻ የሚሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ቀርበውና በሚመለከተው ኃላፊ ታይተው ትዕዛዝ ሊሰጥባቸው ይገባል፡፡

ለ/ ማንኛውም ክፍያ እስከ ብር50,000.00 /ሃምሳ ሺህ/ ድረስ የቴክኒክ ኮሚቴ ውሳኔ ቃለጉባኤ መሰረት በማድረግ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ እንዲሁም ከብር 50,000.00 /ሃምሳ ሺህ/ በላይ ለሆኑ ክፍያዎች እና ከላይ ለተጠቀሰው የቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በሌሉበት የአብይ ኮሚቴ ውሳኔ ቃለጉባኤን መሪት በማድረግ በበላይ አመራሩ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

ሐ/ የክፍያ ግዴታ ከመገባቱ በፊት በቂ የገንዘብ መጠን መኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

መ/ የክፍያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መመርመር ያስፈልጋል፣

- ✓ ክፍያው ተመጣጣኝና ለተገቢው ተግባር መሆኑን፣
- ✓ ክፍያውን ያፀደቀው ሰው ውክልና የተሰጠው መሆኑን፣
- ✓ ለክፍያ የሚፈለጉት ሰነዶች በሙሉ የቀረቡና ሰነዶቹም ዋና ቅጂዎች መሆናቸውን፣
- ✓ የሂሣብ ስሌቱ ትክክል መሆኑን፣
- ✓ በሕግ የታወቁ ታክሶች መቀነሳቸውን ማረጋገጥ፡፡

ሠ/ ክፍያዎችን በቼክ፣ በባንክ ሂሣብ በዝውውር፣ ወይንም ለጥቃቅን ወጪዎች ከተመደበው ገንዘብ ላይ በጥሬ ገንዘብ መፈፀም ይቻላል፡፡

ረ/ ክፍያዎች የሚፈፀሙት ስማቸው በክፍያ ማዘዣው ላይ ለተጠቀሱት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ብቻ ነው፡፡

7) የገቢና የክፍያ ሰነዶች አጠቃቀም፣

1) ሂሣብ አያያዝን በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሒሳብ መዝገብ አያያዝና የገንዘብ ያዥ የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ ይሆናል፡፡

2) ወጪዎችና ገቢዎችን ለመመዝገብም ሆነ ገንዘብ ለመቀበልና ክፍያን ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች/የገቢና የወጪ ደረሰኞች፣ የክፍያ ማዘዣ ቅጾች፣ ወዘተ/ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠቀምባቸው የፋይናንስ ሰነዶች ይሆናሉ፡፡

6. ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የሚተላለፈውን የሥራ ማስኬጃ ሂሣብ በተመለከተ፣

1) ከ6ኛው የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችን ለመሸ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ካለው ሂሣብ ውስጥ የድሬደዋ ከተ አስተዳደር በፅሁፍ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሣብ ቁጥር የተፈቀደው ገንዘብ ይተላለፋ ሆኖም ገንዘቡ ከመላኩ በፊት ዝርዝር ወጪዎቹ በቅድሚያ ቀርበው በአብይ ኮሚቴ መፅደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በቅድሚያ ለድሬደዋ ከተማ አስተዳደር የተፈፀሙ ክፍያዎች በፌዴራል የፋይና አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ወጪ ከተደረጉ በኋላ በሚቀርቡት ሕጋዊ የወ ማስረጃዎች መሠረት መወራረድ ይኖርባቸዋል፡፡

7. የግዢ መመሪያ መርሆዎች፣

1) 6ኛውን የከተሞች ፎረም ለማሳካት የሚያስፈልጉ የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎ በተሟላ መልኩ በማቅረብ ሂደት በግዥ አፈጻጸም ቁጠባን መሰረት ያደረገ የአፈ ብቃትን እና ውጤታማነትን በሚያረጋግጥ፣ የሚፈለገው የአገልግሎትና የዕቃ ዓይ ደረጃውን የጠበቀና ፍላጎትን በሚያረካ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሟላት ፕሮግራ ማሳካት ይሆናል፡፡

2) የሚከናወነው የግዥ ሂደት የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያ የተከ ሲሆን፣ ፕሮግራሙን በማስፈጸም ረገድ በተቋቋመው አቢይ ወይም የቴክኒክ ኮሚ ግዥው ሲፈቀድና ሲጸድቅ የሚከናወን ይሆናል፡፡ በተጨማሪ የሚገዙ የቋሚ ዕቃ በጥንቃቄ እንዲያዙና በቀጣይነት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለቀጣይ ዙር የከተሞ ፎረም በዓላት አከባበር አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ለማድረግ በአግባቡ ተመዝግበ እንዲያዙ ይደረጋል፡፡

3) ፕሮግራሙን ለማሳካት እንዲረዳ የሚያስፈልጉ የአገልግሎትና የዕቃ ግዥን ለማከና በመንግስት የግዥ መመሪያ ላይ በተመለከተው መሰረት የግልጽ ጨረታ፣ የውስን ጨረ የዋጋ ማቅረቢያ እና ከአንድ አቅራቢ የሚፈጸም የግዥ ዘዴዎችን በሥራ ላይ እንዲ ይደረጋል፡፡ የግዥ ዘዴዎቹ በሥራ ላይ ሲውሉ በመንግስት የግዥ አዋጅና መመሪያ በተመለከተው የአፈጻጸም ሂደት ይሆናል፡፡

4) ከከተሞች ፎረም ጋር የተያያዙ ግዥዎችን ለመፈጸም ያስችል ዘንድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ/ ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚውል የአገልግሎትና የዕቃ ግዥ በሚመለከተው ኃላፊ የጸደቀ የዕቃ ግዢ መጠየቂያ ይቀርባል፡፡

ለ/ በሚቀርበው የዕቃና የአገልግሎት የግዥ ጥያቄ መሰረት እስከ ብር 1,500.00 ለሚሆኑ ግዥዎች በቀጥታ ከዕቃው አቅራቢ መግዛት ይቻላል፡፡

ሐ/ ከብር 1,501.00 በላይ ለሆኑ የዕቃ ግዥዎች እስከ ብር 100,000.00 ድረስ፤ ለልዩ ልዩ የአገልግሎት ግዥዎች እስከ ብር 75,000.00 ድረስ፣ ቢያንስ ሦስት የዋጋ ማቅረቢያዎችን ከተለያዩ ድርጅቶች እንዲቀርቡ እና እንዲወዳደሩ ይደረጋል፡፡

መ/ ግዥውን ለመፈጸም ተገቢውን ሰነድ በማዘጋጀት የሚገዛው አገልግሎት ወይም ዕቃ በመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብ መመሪያ መሰረት ይፈፀማል፡፡

ሠ/ ለሚገዛው አገልግሎት ወይም ዕቃ በቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ መሰረት ሰነዶቹን በመገምገም አሸናፊውን በመለየት በግዥ መመሪያው መሰረት እንደአስፈላጊነቱ የውሳኔ ሃሳብ ለግዥ አጽዳቂ ኮሚቴው ወይም ለሚመለከተው ኃላፊ በማቅረብና በማጸደቅ ግዥው ከአሸናፊው ድርጅት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

ረ/ እንደአስፈላጊነቱ አሸናፊው ድርጅት እቃውን እንዲያቀርብ ውል ይዘጋጃል፡፡ በተገባው ውል መሰረት አገልግሎቱ መሰጠቱን ወይም ዕቃው መቅረቡን በሚመለከታቸው የኮሚቴ አባላት ወይም ኃላፊዎች ማረጋገጫ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

ሰ/ የመንግስት መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት በተዘጋጁ ሞዴሎች ላይ የተገዛው ዕቃ ይመዘገባል፡፡

ሸ/ የተገዛውን ዕቃ ጠያቂው ክፍል በሞዴል ወጪ በማድረግ ይረከባል፤ ዕቃውም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ቀ/ የተገዛው ዕቃ ቋሚ ዕቃ ከሆነ የተረከበው አካል በጥንቃቄ በመያዝ ከፕሮግራሙ ፍጻሜ በኋላ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በሞዴል ተመላሽ ያደርጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

በ/ የህትመት ፍላጎቶችን መጠንና ይዘት በሚመለከት የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ለቴክኒክ ኮሚቴ አቅርቦ ካስወሰነ በኋላ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል፡፡

ተ/ ለሽልማትና ለልዩ ልዩ ስጦታዎች የሚውሉ የአቅርቦት ፍላጎቶች መጠንና ይዘት በሚመለከት በቴክኒክ ኮሚቴ ተወስኖ በሚቀርብለት የፍላጎት ዝርዝር መሰረት የግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ግዥ ይፈጽማል፡፡

8. የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት፣

ሀ/ የትራንስፖርት አቅርቦትን በተመለከተ ለኘሮግራሙ ዝግጅት የሚያስፈልጉ የትራንስፖርት ዓይነቶችን በዝርዝር በመለየት የሚሟሉበትን ሁኔታ በዝርዝር በማጥናት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

ለ/ የተዘጋጀውን ፕሮግራም ለማስፈጸም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ለሚፈለገው አገልግሎት ለማቅረብ ካልተቻለ የተሽከርካሪ ፍላጎቶችን በዓይነትና በብዛት በመለየት ለቴክኒክ ኮሚቴው አቅርቦ በማስጸደቅ ከገበያ በኪራይ እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ የተሽከርካሪ አገልግሎት በኪራይ ሲሟሉ የመንግስትን የግዥ እና የፋይናንስ ደንብና መመሪያን በመከተል ይሆናል፡፡

9. የፋይናንስና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ሥራዎች የሚያስተባብር ኮሚቴ፣

የ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ዝግጅትን ለማስፈጸም በተዘጋጀው አጠቃላይ አደረጃጀት መሰረት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ተውጣጥተው በአብይ ኮሚቴ በሚዋቀረው መሰረት ይሆናል፡፡

10. የውሎ አበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች፣

- የውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም በተመለከተ በዐብይ ወይም በቴክኒክ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት ክፍያ ይፈፀማል፡፡
- ለአንድ የከተሞች ሳምንት ተሳታፊ በቀን ብር 400.00 /አራት መቶ ብር/ የውሎ አበል ለሚቆይበት ቀን ተሰልቶ የማይወራረድ ሂሳብ የሚከፈል ሲሆን፣ ይህም አበል የሚቆራረጥ አይሆንም፡፡

- ፕሮግራሙ በሚካሄድበት ወቅት ለሚካሄዱ የፓናል ውይይቶችና ልዩ ልዩ ዝግጅት ተሳታፊዎች የሻይ እና ቡና እንዲሁም የምሳ ወይም የእራት እንደአስፈላጊነቱ ሆለቱንም በአብይ ኮሚቴ ሲወሰን የመስተንግዶ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

- በፕሮግራሙ ላይ ለሚገኙና ሙሉ መስተንግዶና /የምግብና የመኝታ አገልግሎት/ ለሚዘጋጅላቸው አካላት በዐብይ ኮሚቴው ፀድቆ በሚቀርበው ዝርዝርና የቀን ብዛት መሠረት የኪስ ገንዘብ በቀን ብር100.00 /አንድ መቶ ብር/ ይከፈላል፡፡

- የስልክ አገልግሎት ክፍያ በሚመለከት እንደ ስራ ሁኔታ ከየኮሚቴው አባላት ውስጥ ለተለዩት በቴክኒክ ኮሚቴው ሲፈቅድ በቀን፣ በሰው ከብር 50-100 /ከሃምሳ እስከ አንድ መቶ ብር/ድረስ ከአስር ቀን የማይበልጥ ይከፈላል፡፡

- ለጉልበት ሥራ፣ ለቀን ሥራና ለመሳሰሉት ወጪዎች የሚከፈል ገንዘብ በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፀድቀው ሲቀርቡ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

- ከከተሞች ሳምንት ሂሣብ ምርመራ ጋር የተያያዙ ክፍያዎች በአብይ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወየም በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሲፈቀድ ይፈፀማል፡፡ ሆኖም የኮሚቴ ሰብሳቢዎቹ በማይኖሩበት ጊዜ በሚኒስቴር መስርያቤቱ የአሰራር ሥርዓት አግባብ ባለው ኃላፊ ሲፈቀድ ይፈፀማል፡፡

11. የቢሮ ዝግጅት፣

በቴክኒክ ኮሚቴው ለፕሮግራሙ ሥራ ማከናወኛ እንዲረዳ የከተሞች ፎረም በሚካሄድበት በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ለሚከፈተው ጊዜያዊ ቢሮ በተለያዩ የቋሚ ዕቃዎችና የአላቂ ዕቃዎች እንዲደረጅ ይደረጋል፡፡

1) ለጽ/ቤት ሥራ የሚያስፈልጉ የቋሚ ዕቃዎች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚገኙ ከሆነና የመስሪያ ቤቱን መደበኛ ስራ በማያስተጓጉል መልኩ በውሰት በመውሰድ ወይም በዓሉ የሚካሄድበት ከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር እንዲሟሉና በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

2) በግዥ መሟላት የሚገባቸው የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ከሆኑ የግዥ ሂደቱን ተከትሎ እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማት ፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Urban Development Housing & Construction

12. የመመዝገቢያ ክፍያ፣

1) በ6ኛው የከተሞች ፎረም ኤግዚቢሽን ላይ ቢያንስ ከ150 እስከ 180 ከተሞች ይመዘገባሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የምዝገባው ክፍያ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በከተማ ወይም በተሳታፊ ድርጅቱ ይሆናል።

2) የምዝገባ ጊዜውን በተመለከተ ተመዝጋቢ ከተሞች ክፍያቸውን እስከ መስከረም 30 ቀን 2006 ዓ.ም. ድረስ ማጠናቀቅ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ከተሞቹ የሚፈለግባቸውን የምዝገባ ክፍያ በሚከተለው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

" በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር የከተማ ኘላን፣ ፅዳትና ውበት ማስተባበሪያ ቢሮ ስም በተከፈተው የባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000000985027 ወይም 0171530950600 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ" ይሆናል።

13. የኤግዚብሽን ቦታ /ድንኳን/ ኪራይ አከፋፈል፣

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም በህዳር ወር 2007 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ይካሄዳል።

1) ለዚህም ከተሞች ለሚያዘጋጁት ኤግዚቢሽን ለድንኳን ኪራይ እና ለመሳሰሉት በካሬ ሜትር ብር 150.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ብር/ መክፈል ይኖርባቸዋል።

2) የድንኳኖቹም ስፋት ከ12 እስከ 500 ካሬ ሜትር ይሆናል።

3) ከተሞች በካሬ ሜትር የሚፈለግባቸውን ሂሣብ ኤግዚቢሽኑን በሚያሳዩባቸው ቀናት ልክ አስልተው እስከ መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም. ድረስ ቀደም ሲል በተጠቀሰው የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

14. ከስፖንሰሮች የሚገኝ ገቢን በተመለከተ፣

ከዚህ ፕሮግራም ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማትና ድርጅቶች በማፈላለግ ለዝግጅቱ የሚሆን ገንዘብ ለሚያሰባስብ በተቋቋመው የስፖንሰር አፈላላጊ ኮሚቴ በኩል በሚቀርብ የቃል ኪዳን ፎርምና ዝርዝር መሰረት ገቢ ይደረጋል።

15. ሂሣብ ማስመርመር፣

1) የከተሞችን ፎረም ሂሣብ እንቅስቃሴ የተሟላ ሪፖርት በማዘጋጀት ህጋዊ ፈቃድ ባለው የውጪ ኦዲተር እንዲመረመር ይደረጋል፣

2) የከተሞች ሳምንትን አስመልክቶ የተደረገው የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሂሳብ በሶስት ወራት ውስጥ ይዘጋል።

3) የከተሞች ፎረምንን ሂሳብ አስመልክቶ ሂሳቡ ከተዘጋበት ቀጥሎ በሚገኙት ሶስት ወራት ውስጥ በኦዲተሮች ምርመራው ተጠናቆ ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

16. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ፣

ይህ መመሪያ ለከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር ቀርቦ ከጸደቀበት ከመስከረም 19 ቀን 2007ዓ/ም ጀምሮ የ6ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ፎረም ሂሳብ ተመርምሮ እስከ ሚዘጋበት ድረስ በስራ ላይ ይውላል።

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
ሚኒስትር